# ክብረ ቅዱሳት ሥዕላት

እንደሚታወቀው ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ የማይታይና የማይዳሰስ ረቂቅ መንፈስ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም (የሚያመልኩትም) በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል» ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው
ትምህርት ዐቢይ ማስረጃ ነው (ዮሐ. 4፤24)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የጌታችንን ትምህርት ተከትሎ እግዚአብሔር መንፈስ (ረቂቅ) መሆኑን ሲናገር፤ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ» ብሎአል (2 ቆሮ.3፤ 17)።

በዚሁ መሠረት የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑት ቅዱሳን መላእክትም ረቂቃን መናፍስትም መሆናቸው የታወቀ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን ያረጋግጥልናል (መዝ. 103 (104)፣4)።

<u>**ጥያቄ፤** ከዚህ በላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ረቂቅ መንፈስ ከሆነ፤ አገልጋዮች ቅዱሳን መላእክትም ረቂቃን መናፍስትም ከሆኑ፤ እግዚአብሔርንም ሆነ መላእክትን በሥዕል መግለጽ ይገባልን? እግዚአብሔር ይህንን ይመስላል፣ መላእክቱም ይህን ይመስላሉ እያሉ እነሱን በስዕል እየሳሉ መግለጽ ተገቢ ነውን?</u>

**መልስ፤** እግዚአብሔር በባሕርዩ (በመለኮቱ) በስዕል ወይም በቅርጽ መግለጽ ፈጽሞ አይገባም፤ ወይምሰማይና ምድርን የመላውን እግዚአብሔርን በመተው ስዕል እየሳሉ፤ ቅርጽ እየቀረጹ አማልክትን (ጣዖታትን) ማምለክ ዐቢይ ኃጢአት መሆኑን ራሱ እግዚአብሔር ለሙሴ አዞታል እንዲህ ብሎ፤ «ከግብጽ ከባርነት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ፤ በላይ በሰማይ ካለው ፤ በታችም በምድር ካለው ነገር የማናቸውም ምሳሌ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፤ አትስገድላቸውም፤ አታምልካቸውም፤ በሚጠሉኝ እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምህረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ» (ዘጸአ. 20፤1-6)።

ነገር ግን እግዚአብሔር ለወዳጁ ለአብርሃም በሦስትነቱ ምስጢር ሦስት መንገደኞችን መስሎ እንደተገለጠለት መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ዘፍጥ. 18፤ 1-15)። ስለዚህ ይህንን ታሪክ በሥዕል መግለጽ የሚገባ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን «የአብርሃም ሥላሴ» በሚል ርእስ በሥዕል እየገለጸች ስታስተምርበት ትገኛለች።

ቅዱሳትን መላእክትም በአምሳለ ሰብእ ማለት በሰው አርአያ ለእስማኤል እናት ለአጋር (ዘፍጥ. 16፤7) ለያዕቆብም (ዘፍጥ. 32፤1) ለበለዓምም (ዘኁል. 22፤31) ለኢያሱም (ኢያሱ 5፤13)፤ ሰውን መስለው ስለ ተገለጹላቸው የእነሱን መገለጽ፣ ተራዳኢነታቸውንና ታዳጊነታቸውን ለምእመናን ለመግለጽ ታሪኩን
በሥዕል ማቅረብ የሚገባ ነው። በመሆኑም በኦሪት ዘጸአት በምዕራፍ ሃያ ከተጻፈው ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር የሚቃረን አይደለም። በሰው አምሳል በመሣልና ለእነሱም የጸጋ (የአክብሮት) ስግደት ማቅረብነቢዩን ኢያሱን መምሰል ነውና የሚገባ ነው (ኢያሱ 5፤ 13)።

ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ሦስቱን ወጣቶች ከተወረወሩበት የእሳት ጉድጓድ ያዳናቸውን ቅዱስ ገብርኤልን በሥዕል ሥሎ ማቅረብ የእምነት ሥራ እንጂ የኃጢአት ሥራ አይደለም (ዳን. 3፤ 1-30)። ወደ እሳት የተጣሉትንም ምእመናን ከእግዚአብሔር ተልኮ ላዳነ ለእግዚአብሔር መልአክ ሥዕል የአክብሮት ስግደት ማቅረብ ሥርዓተ ሃይማኖትን መፈጸም ነው እንጂ መናፍቃኑ እንደሚተቹት ጣዖት ማምለክ አይደለም። ንጉሱ ናቡከደነፆርም መልካም ነገር ለሠራለት ለነቢዩ ዳንኤል ተደፍቶ የጸጋ ስግደት እንዳቀረበለትና ይህንንም በማድረግ እንዳልተወቀሰ፤ እውነተኞቹ ምእመናንም በተራዳኢውና በአማላጁ በቅዱስ ገብርኤል ሥዕል ፊት ተደፍተው የአክብሮት ስግደት ቢያቀርቡለት የእግዚአብሔር ወገኖችና የቅዱስገብርኤል ወዳጆች ያሰኛቸዋል እንጂ አያስወቅሳቸውም (ዳን. 2፤ 46)።

ሥዕልን ዕጣን የአምልኮት መግለጫዎች እየሆኑ እንደሚቀርቡ የታወቀ ነገር ነው። ለምሳሌ ሥዕል በሕገ ወጥ ተጠቃ ሚዎች የጣዖት መግለጫ እየሆነ ይቀርብ እንደ ነበር ከነቢዩ ሕዝቅኤል እንረዳለን። (ሕዝ. 8፤ 7-13)።

ስለሆነም በነቢዩ አገላለጽ ኃጢአትና በደል ሆኖ የተቆጠረው ሥዕሉ ሳይሆን በሥዕሉ አማካይነት አምልኮ ጣዖት መ ፈጸሙ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሠራዊት የሆኑትን ቅዱሳን መላእክትን በሥዕልም ሆነ በቅርፅ አዘጋጅቶ ማቅ ረብ መፈቀዱን ከኦሪቱና ከመጽሐፈ ነገሥት መረዳት እንችላለን። ነቢዩ ሙሴና ንጉሡ ሰሎሞን የእግዚአብሔር አገ ልጋዮች የሆኑትን ኪሩቤልን በወርቅ አዘጋጅተው በታቦቱ መክደኛ ላይ እንዲያስቀምጡ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ዘጸአ. 25፤ 18 ፣ መጽ. ነገ. 8፤7)።

ስለዚህ ጨረቃ በከዋክብት ታጅባ ስትታይ እጅግ እንደምትደምቅ፤ ተራራም በዝናብ ወራት በአበባ ተሸፍኖና ደምቆ ሲታይ እንደሚያምር ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር አገልጋዮች በሆኑት በቅዱሳን መላእክት፤ በጻድቃንና በሰማ ዕታት ሥዕሎች አሸብርቃና ደምቃ ስትታይ በእርግጥ የእግዚአብሔር መንበር (ዙፋን) ያለባት የእግዚአብሔር ቤት መሆንዋን በበለጠ መረዳት እንችላለን።

## ከሥዕል የሚገኙ ዐበይት ጥቅሞች

የጥንቱና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሚከተል ክርስቲያን ሁሉ ከቅዱሳት ሥዕሎች ሁለት ዐበይት ጥቅሞችን ያገኛል ። ይኸውም ትምህርትና ረድኤት ናቸው።

ትምህርት በሥዕሎች አማካይነት የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በምሕጻረ ቃል በጐላና በተረዳ ሁኔታ ማጥናትና ማወቅ ይቻላል። በኦሪት ዘፍጥረት በሁለተኛውና በሦስተኛው ምእራፍ የተገለጸው የአዳምና የሔዋንአፈጣጠር በእባብና (በሰ ይጣን) አሳችነት በኃጢአት መውደቅ በሥዕል ሲገለጽ የበለጠ መረዳት ይቻላል። በዚሁ ዓይነት አብርሃም ልጁን ይ ስሐቅን ለእግዚአብሔር ሊሰዋው ሲዘጋጅና እግዚአብሔርም በይስሐቅ ፈንታ በጉን እንዳቀረበለት በሥዕል ሲገለጽ ታ ሪኩ የበለጠ ግልጽ ይሆናል (ዘፍ. 22፤1-14)።

ይልቁንም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረው ቃለ እግዚአብሔር (አካላዊ ቃል) በኋለኛው ዘመን ሰውን ለማዳን ወደዚ ህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ ከሥጋዋ ሥጋን ፣ ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ ከኃጢአት ብቻ በቀር ፍጹም ሰው ሆኖ በድንግልና የተወለደውና ተሰቅሎ በሞቱ ዓለሙን ማዳኑን በሥዕል ገልጾ ማቅረብ መስበ ክ፤ ማስተማር ነው። በዚህም መሠረት የጌታችንን የልደቱን ታሪክ፣ የጥምቀቱን ታሪክ፣ የስቅለቱን ታሪክ፣ የትንሣኤ ውንና የዕርገቱን ታሪክ በሥዕል ነድፎ ለምእመናንማቅረብ ማለት የጌታችንን ወንጌል መንግሥት መስበክና ማስተማር ማለት ነው።ምክንያቱም ሥዕል ራሱበጉልህ የተጻፈ ጽሑፍ ማለት ነውና። ጌታችን ተወለደ፣ ተጠመቀ፣ ተሰቀለ ፣ ሞተ፣ ከሙታን ተለይቶተነሣ... የሚለው የወንጌሉ ታሪክ በሥዕል ማቅረብ ማለት ታሪኩን በጉልህ ጽፎ ማቅረብ ማለ ት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች ተግሳጽ ሲጽፍ «የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፤ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር» ያለው ኢየሱስና ታሪኩን በሚገባ አውቀውትና ከልብም ተረድተውት እንደ ነበር ለመግለጽ ነው (ገላ.3፤ 1-2)።

ስለዚህ ከላይ እንደተገለጸው ቅዱሳት ሥዕሎች በመመልከትና ልብ ብሎ በማንበብ (በማስተዋል) ታሪኩን በሚገባ ማ ወቅና መረዳት ስለሚቻል ፤ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ሥዕሎች የክርስትና ሃይማኖት አስተማሪዎችና አስረጂ ዎች መሆናቸውን መገንዘብ ተገቢ ነው።

ሁለተኛው ጥቅም ከቅዱሳት ሥዕሎች የሚገኘው ሌላው ዐቢይ ጥቅም ደግሞ ረድኤት (ርዳታ) ነው።

በሕይወተ ሥጋ ያለ ማንኛውም ሰው ይኑሩም ይሙቱም የዘመዶቹን ፎቶግራፍ በቤቱ፤ በመኝታ ቤቱ ወይም በቢሮው ይሰቅላል፤ ወደ ተሰቀለውም ፎቶግራፍ በየጊዜው ያተኩራል፤ ይኸውም አንደኛ ፍቅሩን ለመግለጽ፣ ሁለተኛ ለማሰብና ለማስታወስ ነው። በዚሁ መሠረት በሥርዓተ ሃይማኖትም ምእመናን የክርስቶስን፣ የቅድስት ድንግልን፣ የመላእክትን፣ የጻድቃንን የሰማዕታትን ሥዕሎች በቤተ ክርስቲያን፣ በቤታቸው፣ በጸሎት ቤታቸው፣ በጸሎት መጻሕፍቶቻቸው የሚያደርጉት፤ አንደኛ ፍቅራቸውን ለመግለጽ፣ ሁለተኛ ለማሰብና ለማስታወስ፣ ሦስተኛ ከሥዕሎቹ ባለቤቶች ርዳታን፣ እገዛን ፣ ምልጃንና በረከትን ለመቀበል ነው።

ለምሳሌ- በጌታችን ሥዕል ፊት ቆሞ መጸለይ ከጌታ ምሕረትንና ይቅርታን ለመቀበል ነው። ጌታችን በመስቀሉም ሆነ በሥዕሉ አማካይነት ይቅርታን ምሕረትን ይሰጣል። እንደሚሰጥም በዚሁ የተጠቀሙትንምእመናን ጠይቆ መረዳት ይቻላል። በቅድስት ድንግልን፣ በቅዱሳን ሥዕሎች ፊት ቆሞ በመጸለይም የሥዕሎቹ ባለቤት ከሆኑት ርዳታን፣ እገዛን ፣ በረከትን ለማግኘት ነው። ለዚሁም ምስክሮቹ በጌታና በቅድስት ድንግል ሥዕሎች፣ በቅዱሳን መላእክትና በቅዱሳን ሰማዕታት፣ በጻድቃን ሥዕሎች እየተማጸኑ ከፍተኛ ርዳታንና በረከትን የተቀበሉትን ካህናትና ምእመናን ጠይቆ መረዳት ይገባል። ነገር ግን ዝም ብሎ መንቀፉ ጉዳትን እንጂ ጥቅምን የማይሰጥ መሆኑን መረዳት ይገባል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለነበረበት በጣም ቅርብ የነበሩት የጥንት ክርስቲያኖች በጌታችን ሥዕል፣ በቅድስት ድንግል ሥዕልና በቅዱሳን ሥዕሎች ይማፀኑ እንደ ነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል። በዘመናችን ተቆፍረው የተገኙ የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ፍርስራሶችም በሥዕላተ ቅዱሳን መማፀን ጥንታዊ ትውፊት (ሥርዓት) እንደሆነ ያመለክታሉ።

ታሪክን መካድ ደግሞ አያትና ቅድመ አያትን መካድ ማለት ነው። ስለ ሥዕል ክብር የቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ታሪክ ምስክር ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው በታሪክ መንገድ መሆኑ የታወቀ ነው። በዚሁ መሠረት የታወቀው ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ ኤጲስ ቆጶስዘቂሳርያ ስለ ጌታ ሥዕል አጀማመርና አመጣጥ ጽፎ ያቀረበውን ብፁእ አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘሸዋበመጽሐፋቸው ጠቅሰውታል። እኛም የጥቅሱን ፍሬ ነገር ቀጥለን ጠቅሰነዋል።

«ንጉሥ ዐብጋር በውር (ኤዴሣ) ከተማ የአገሩ ንጉሥ በመሆን ጌታችን በነበረበት ዘመን ይኖር ነበረ፤ ስሙም (ልዑካን) ይባል ነበር። ዐብጋር ማለት በከለዳውያን ቋንቋ ቈሣር ማለት ነው። ዐብጋር በዚያ ዘመን በጠና ታሞ ነበር፤ የጌታችንን ተአምራት በዝና ሰምቶ ይፈውሰው ዘንድ ደብዳቤ ጽፎ ለጌታችን ላከለት፤ ጌታችንም ደብዳቤውን ከመልእክተኛው እጅ ተቀብሎ ካነበበው በኋላ «ሳያየኝ ያመነኝ ዐብጋር ብፁዕ ነው» ብሎ ዐብጋርን በማመስገን በሱ ስም እንዲፈውሰው ከደቀ መዛሙርቱ መካከል አንዱን እንደሚልክለት በመግለጽ መልስ ላከለት። ነገር ግን ከጌታ ጋር ተገናኝቶ የተመለሰው የዐብጋር (ዩካማ) መልእክተኛ ሠዓሊ ስለነበር ከጌታችን ጋር ሲነጋገር ፊቱን በሥዕል ነድፎ (ሥሎ) ከደብዳቤው ጋር ይዞ ተመለሰ። ከዚያም እንደ ደረሰ ከጌታ የተላከውን ደብዳቤ ለታመመው ንጉሥ አነበበለት፤ ሥዕሉንም አሳየው። በዚያን ጊዜ በሽተኛው ንጉሥ የጌታችንን ቃል ከደብዳቤው ሰምቶና ሥዕሉንም በዓይኑ ተመልክቶ ወዲያው ከሕመሙ እንደ ተፈወሰ ታሪኩ ያስረዳል (አባ ጎርጎርዮስ፤ የኢ. ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያንታሪክ 1974 ገጽ 119- 120)።

እንደገናም ይኸው አውሳብዮስ ስለ ጌታችን ሥዕል የሰጠው ምስክርነት እንዲህ የሚል ነው «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ደሙን እያንጠፈጠፈ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጎልጎታ በሚጓዝበት ወቅት እያለቀሱ ከሚከተሉት ደጋግ ሴቶች መካከል ቬሮኒካ የተባለች ደግ ሴት የራስዋን መሸፈኛ አውልቃፊቱን እንዲያድፍበት (እንዲጠርግበት) ለጌታ ወረወረችለት፤ ጌታችንም በደምና በላብ የተጠመቀውን ፊቱን ጠርጎ ሲመልስላት ሥዕለ ገጹ ማለት የፊቱ መልክ በሻሽዋ ላይ ታትሞ ቀረ» በማለት ከላይ የጠቀስነው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ ይመሰክራል።

ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ደግሞ ወላዲተ አምላክ በነበረችበት ክፍለ ዘመን የነበረው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ የጌታን ታሪክ (ወንጌል) ሲጽፍ ስለ ወላዲተ አምላክም ብዙ ጽፎአል። በዚህ የያዕቆብ ወንጌል (ያዕቆብ ታሪክ) በተባለው የትውፊት መጽሐፍ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ለመጀመሪያ ጊዜ የማርያምን ሥዕል መሣሉ ተጽፎአል።

አውሳብዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘቂሳርያና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እንደ መሰከሩት የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል ፣ ለወላዲተ አምላክ፣ ለቅዱሳን መላእክት፣ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ሥዕሎች ከፍ ያለ ክብር እንዲደረግላቸውና የጸጋና የአክብሮት ስግደት እንዲቀርብላቸው ስታስተምር ኖራለች። ምእመናንም በቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት በሚጸልዩበት ቤተ ክርስቲያንና በቤታቸው በሚገኘው በግል ጸሎት ቤታቸው የጌታችንን፣ የቅድስት ድንግል ማርያምና የቅዱሳንን ሥዕሎች በግድግዳው በመስቀልና የክብር ስግደት በማቅረብ ሲማፀኑባቸው ኖረዋል።

በዚሁ ሁኔታ የሥዕል ክብር በጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተጠበቀ እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ከቆየ በኋላ ሳይታሰብ በድንገት ከክርስቲያኖቹ መካከል ጥቂቶች ሰዎች የሥዕልን ክብር በመቃወም ተነሡ። በዚሁ ምክንያት በሮምና በቢዛንታይን ግዛቶች ከባድ ክርክርና ሁከት ተቀሰቀሰ። በዚህ ጊዜ በ797 ዓ.ም የምስራቅ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጉባዔ አድርገው የቅዱሳንን ሥዕሎችማክበርና መሳም (መሳለም) እንደሚገባ ለሥዕሎቹም የአክብሮት ስግደት ማቅረብ ተገቢ መሆኑን በሰፊው አትተው ወስነዋል። እንሆ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፕሮቴስታንቶች እስከ ተነሡበት እስከ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ የሥዕል ክብር ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ቆይቶአል። በአሁኑ ክፍለዘመንም በመላው ዓለም በሚገኙ ከሦስት መቶ ሚልዮን በላይ በሚሆኑ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖችና ከዘጠኝ መቶ ሚልዮን በሚበልጡ ካቶሊካውያን ክርስቲያኖች ዘንድ የሥዕል ክብር ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል።

እነዚህ ከአንድ ሺህ አራት መቶ ሚልዮን በላይ የሚሆኑ የዓለም ክርስቲያኖች በሙሉ በአካል ሦስት በመለኮት (በአምላክነት) በባሕርይ አንድ አምላክ ብቻ የሆነውን እግዚአብሔርን እያመለኩ ለቅድሰት ድንግል ፣ ለቅዱሳን መላእክት፣ ለጻድቃንና ለሰማዕታት፣ ለቅዱስ መስቀልና ለቅዱሳት ሥዕሎች የጸጋና የአክብሮት ስግደት ያቀርባሉ፤ ለሥዕሎች ተማኅጽኖ እያቀረቡ የሥዕሎቹ ባለቤቶች ከሆኑት ከጌታችንና ከቅዱሳን ዘንድ ርዳታን፣ በረከትን እገዛን ያገኛሉ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉና በሥዕሉ አማካይነት ምሕረቱንና ቸርነቱን ይስጠን። ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፣ ቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃንና ለሰማዕታትም በሥዕላቸው አማከይነት በረከቱንና ረድኤትን ከጌታ ዘንድ እያማለዱ እንዲያሰጡን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልን «አሜን»።

አቡነ ገብርኤል በ1990 ካሳተሙት «ክብረ ቅዱሳን» ከሚለው መጻሕፍ የተወሰደ።